ሳምንታዊ ዜና ዘገባ

ፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምፅ ራዲዮ መጋቢት 27 ቀን 2001 ዓ.ም.

- ኢሕአፓ በአለም አቀፍ ደረጃ ከፍተኛ የዲፕሎማሲ እንቅስቃሴና ግንኙነት በማካሄድ ላይ ይገኛል ተባለ፣

- ታላቅ የተቃዉሞ ሰልፍ በእንግሊዝ አገር ሎንዶን ከተማ ተካሄደ፣ መለስ ዜናዊ በሎንዶን ከተማ በመጋለጡና ታላቅ ቅሌትና ሀፍረት በመከናነቡ በሎንዶን ሊያደርገዉ የነበረዉን የፕሬስ ኮንፈረስ (ጋዜጣዊ መግለጫ) ለመሰረዝ መገደዱ ተጋለጠ፣

- የወያኔ አገዛዛ የቡና ንግድን በሰበብ ባስባቡ በራሱ ቁጥጥር ስር ለማስገባት እርምጃ እየወሰደ ባለበት በአሁኑ ወቅት ከ20 ሺህ ያላነሱ የከተማ ጽዳት ሴት ሰራተኞችን ከስራና ከገቢ ለመነጣጠል እየተንቀሳቀሰ መሆኑም ተነገረ፣

- ወያኔ የተባይ መግደያ፣ ማዳበሪያ፣ ሰዉ ሰራሽ ዘር እያለ በሚያሰራጨዉ ሁሉ የኢትዮጵያ መሬትና የእርሻ ምርት እየተጎዳ መሆኑ ተጋለጠ፣ ጃፓንም ቡና አልገዛም ያለችበት ምክንያት የተባይ መግደያ ርዝራዥ በማግኘቷ መሆኑ ተነገረ፣

- ለጅቡቲ የኤሌክትሪክ ኃይል አያቀረበ ያለዉ ወያኔ በከተሞች መብራት ኃይል በፈረቃ ማደሉ ሲታወቅ የግልገል ግቤ ተጠቃሚ የተባለችዉ ኬንያ የለሁበትም አለች፣ ግድቡን የሚገነባዉ የጣሊያኑ ኩባንያ ሳልኮስት ለወያኔ ባለስልጣናት ጉቦ መስጠቱ ተጋለጠ፣

- አዜብ ጎላ የወያኔ የኢኮኖሚ ተቋም ኤፈርት ምክትል ኃላፊ ሆና ተሾመች፣ እርሷ የተካችዉ የቀድሞ የወያኔ የኢኮኖሚ አለቃ ስብሃት ነጋ የተለመደ ሴራዉን በመለስም ላይ ያደርግ እንደሆነ ገና አልታወቀም፣

- በኢትዮጵያ የሀሰት ብር ያዝኩ የሚለዉ ወያኔ እርሱ ያሰራጨዉ መሆኑ ተነገረ፣ በፈረንሳይ የሚታተመዉ የኢትዮጵያ ፓስፖርተም ዉስጥ ለዉስጥ እንደሚሸጥ ታወቀ፣ የሚሉና ሌሎችም ይገኙበታል።

ሙሉዉን ከሚቀጥለዉ ገጽ ጀምረዉ ያንብቡ<<<>>>

## ኢሕአፓ በአለም አቀፍ ደረጃ ከፍተኛ የሆነ የዲፕሎማሲ እንቅስቃሴና ግንኙነት በማካሄድ ላይ ይገኛል

ከኢሕአፓ ከፍተኛ አመራር ኮሚቴ የደረሰን ዜና እንደሚያመለክተው ከሆነ ኢሕአፓ በአለም አቀፍ ደረጃ ከፍተኛ የሆነ የዲፕሎማሲ እንቅስቃሴና ግንኙነት በማካሄድ ላይ ይገኛል።

ይህ የዲፕሎማቲክ እንቅስቃሴ ልዩ ትኩረት ያደረገበትም በአውሮፓ፡ በሰሜን አሜሪካና ካናዳ፡ በኒውዜላንድና አውስትራሊያ፡ ተጽዕኖ ለሚኖራቸው በአፍሪካና በመካከለኛው ምስራቅ ለሚገኙ መንግሥታት፡ አህጉራዊ ተቋማት ለሆኑ እንደ አውሮፓው ሕብረትና የአፍሪካ አንድነት ድርጅት እንዲሁም ከኢትዮጵያ ጋር በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ግንኙነት ላላቸው የእድገትና የገንዘብ ብደር ሰጪ ተቋማት የፖለቲካ ድርጅቶች፡ ለተለያዩ መንግሥታዊ ላልሆኑ የሲቪል ድርጅቶች በተለይም በኢትዮጵያ ውስጥ በግብረ ሰናይ ተግባራት እየተንቀሳቀሱ ለሚገኙት ድርጅቶች ላይ ነው።

ለዚህም ሕዝባችን ለደረሰበት የፖለቲካ፡ ማህበራዊና ኤኮኖሚያዊ ቀውስ ዋና ተጠያቂ የሆነውን የወያኔን አገዛዝ በትግሉ አስወግዶ ሰላምንና የተረጋጋ ማህበራዊ ሥርአት ለመመስረት በሽግግር ሂደት ማለፍ እንደሚገባ የሚተነትንበት ዴሞክራሲያዊ የመፍትሄ አማራጭ አዘጋጅቶ በአድራሻዎቻቸው በመላክ ላይ ይገኛል። በተቻለበትና ፍቃደኝነት በታየበት ደግሞ መልዕክተኛ በመላክም ስለ ወቅቱ ሁኔታም ሆነ በቀረበው ዴሞክራሲያዊ አማራጭ ትንታኔ ዝርዝር ገለጻ በመስጠት እየተደረገ ያለ እንቅስቃሴ መሆኑም ታውቋል። ይህ የዲፕሎማቲክ እንቅስቃሴ በ2010 ዓ.ም. ለታሰበው ለወያኔ የምርጫ ጨዋታ ድረስ ተጠናክሮ እንደሚቀጥልም ታውቋል።

በተጨማሪም "*ኢትዮጵያ - ዴሞክራሲያዊ አማራጭ - ችግሮቿና የወደፊት እጣዋ*" በሚል ርዕስ ያዘጋጀው ይህ 15 ገጽ ያለው ጽሁፍ የበርካታዎችን ትኩረት እንደሳበና ቀጣይ ውይይትም ለማድረግና ለሂደቱም የተቻላቸውን አስተዋጽዖ ለማበርከት ፍቃደኝነታቸውን የገለጹ መኖራቸውም ተገልጿል።

ጹሁፉ ባለፉት ሰላሳ ስድስት አመታት ውስጥ ለሽግግር ሂደት ይጠቅማሉ ተብለው የቀረቡ መፍትሄዎችን ያስታውሳል። በርግጥም በጹሁፉ እንደተገለጸው በ1974 ዓ.ም. ሕዝባዊ አብዮታዊ እንቅስቃሴ በተካሄደበት ወቅት ለዴሞክራሲና ሰብአዊ መብቶች መከበር የተደረገው ትግል የጦር

ሀይሉን በመጠቀም በደርግ ሊጨናገፍ በነበረበት ወቅት “ጊዜያዊ ህዝባዊ መንግሥትን” በአማራጭነት አቅርቦ ተግባራዊ ሳይሆን መቅረቱ በሀዘኔታና በቁጭት የምናስታወሰው ነው። ከዛ በኋላም ቢሆን ኢሕአፓ በተከታታይ ሳይታክት ለሂደቱ መፍትሄ የሚሆን አማራጭ ሃሳቦችን እንደ ኢሕአፓም ሆነ በአባላነት በተዋቀረበት የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ቅንጅትና ኅብረትም አማካኝነት ተመሳሳይ መፍትሄ ማቅረቡ የሚታወስ ነው። በፌብሩዋሪ 2001 ዓ.ም. እንደ አውሮፓ አቆጣጠር “የሽግግር አደረጃጀት በኢትዮጵያ□ የኢሕአፓ ፖሊሲ “ በተሰኘ ርዕስ ያቀረበው ጽሁፍ በምሳሌነት ሊጠቀስ የሚችል ነው።

በዲሴምበር 1989 ዓ.ም. የመንግሥቱ ኃ/ማሪያም ወታደራዊ አገዛዝ ማክተሚያው በደረሰበት ወቅት ሁሉኑም የፖለቲካና ህዝባዊ ድርጅቶችን ያቀፈ፡ ዝርዝር ተግባሩና የሥልጣን ዘመኑ በግልጽ የተቀመጠ “የሽግግር መንግስት እንዲቋቋም” ሃሳብ አቅርቦ እንደነበርም ይታወሳል።

ኢሕአፓ የወታደር አገዛዙና በጊዜው የሱ ተቃዋሚ ነኝ ይል የነበረው ወያኔ ለዚህ ሽግግር ሂደት ከፍተኛ እንቅፋት እንደሚሆኑ ግልጽ አድርጎ ነበር። እንደሚታወሰውም ወያኔ ኢትዮጵያዊ ካባ በማጥለቅ ከባዕዳን ኃይሎች በተለይም ከአሜሪካና ከ እንግሊዝ ጋር በመመሳጠር ሂደቱን አደናቅፎ ይኸው አሁን ያለንበት ደረጃ ላይ እንገኛለን።

በአሁኑ ወቅት ወያኔ በሁሉም አቅጣጫ ተወጥሮ ይገኛል። ይህም ቀሰ በቀስ መውደቂያውን እያፋጠነ እንደሚሆን ግልጽ ነው። በመሆኑም ሰርገኛ መጣ በርበሬ ቀንጥሱ እንዳይሆን ከወዲሁ መዘጋጀትን የግድ የሚል መሆኑ ሁኔታዎች ይጠቁማሉ። ይህንን ከግንዛቤ በመውሰድ ኢሕአፓ ለሽግግር ሂደት የሚሆን አማራጭ መፍትሄ የበኩሉን አቅርቦ ዲፕሎማሲያዊ እንቅስቃሴ እያካሄደ ይገኛል። የቀረበ አማራጭ መፍትሄ በቀላሉ ስምሪት የማያገኝ መሆኑንም ይገነዘባል። ሕዝባችንም ሆነ ኢትዮጵያዊ ታጋይ ድርጅቶች በርካታ ውጣ ውረዶችን በግዴታ ማለፍ እንደሚኖርባቸውም ግልጽ ነው። ኢሕአፓ በዚሁ ጽሁፉ ለብዥታ በማያመች መልኩ ስለ ዴሞክራሲ ያለውን ግንዛቤ በስፋት አቅርቧል። በዚህ ትንታኔው በመመስረትም የሽግግር ሂደቱ ምን መልክ ሊይዝ እንደሚችል ያብራራል። ሊጠቃለሉ የሚችሉ ኃይሎችንም በአይታው አስገብቶ ይተነትናል። ወያኔ በዚህ ሂደት መጠቃለል መቻል አለመቻሉን የፖለቲካ ሥልጣን ከመያዙ በፊትም ሆነ በኋላ የሰራቸውንና እየሰራቸው ያሉትን ተግባራቱን እማኝ በማድረግ የራሱን አስተሳሰብ አቅርቧል። የመውጫ ሁኔታንም ጠቁሟል። የሚመለከታቸው ኢትዮጵያዊያን ሀገር ወዳድ ኃይሎች ይህንን ጽሁፍ

ተመልክተው በመወያየት ተገቢውን እርምጃ መውሰድም የሚጠበቅባቸው ይሆናል። ለዚህም ይረዳ ዘንድ በተለያዩ ድረገጾች ላይ እንዲታተም መደረጉ ታውቋል። ወጣም ወረደም ግን ወያኔን ለመጣልና ለማስወገድ ትግል መጠናከር እንዳለበት ኢሕአፓ ያሳስባል።

**ባለፈዉ ሐሙስ መጋቢት 24 ቀን 2001 ዓ.ም. ፣ በእንግሊዝ አገር በሎንዶን ከተማ ታላቅ ሕዝባዊ የተቃዉሞ ሰልፍ ተካሄደ።**

በኢንዱስትሪ የበለፀጉ ሃያ አገራት፣ በዓለም ላይ የደረሰዉን የኢኮኖሚ ቀዉስ አስመልክቶ በመፍትሔ ሀሳብ ላይ ለመነጋገር በጠሩት ስብሰባ የተገኘዉን መለሰ ዜናዊን በመቃዎም ከየቦታዉ በየቡድኑ የተሰባሰበዉ ኢትዮጵያዊ ኃይል ንዴቱንና ቁጭቱን ሲያሰማ ዉሏል።

በዕለቱ ከተያዙትና ከተሰሙት መፈክሮች ዉስጥ

- ወያኔ ለስልጣን ከመብቃቱ ጀምሮ ደብዛቸዉን ያጠፋቸዉ እነፀጋዬ ደብተራዉ፣ስጦታዉ ሁሴን፣ አበራሽ ይበርታእና ሌሎቹም ይፈቱ፣
- ድምፃዊዉ ቴዲ አፍሮ ይፈታ፣
- ብርቱካን ሚዴቅሳ ትፈታ፣
- በወያኔ እስር ቤት በመማቀቅ ላይ የሚገኙ በሺዎች የሚቆጠሩ የፖለቲካ እስረኞች ይፈቱ፣
- መለስ የዘር ማጥፋት ወንጀለኛ ነዉ፣
- ሞት ለወያኔ፣ ወያኔ ፀረ ሕዝብና ፀረ ኢትዮጵያ ነዉ፣
- ዴሞክራሲ ለማያውቅ መንግስት እርዳታ ይነፈገዉ፣ የሚሉና ሌሎቹም ይገኙበታል።

በተጨማሪም ወያኔ ገደል ይግባ ሆ ሆ ሆ ሆ ፤ የወያኔ ኑሮ ለየለት ዘንድሮ፤ እና የመሳሰሉት ዜማዎችም ተደምጠዋል።

ይህ የተቃዉሞ ሰልፍ በርካታ የዉጭ አገር ዜጎችን ቀልብ የሳበና የእንግሊዝ አገርና ከዚያም ዉጭ ያሉትን የዜና አዉታራትን ትኩረት የሳበ እንደነበረ ለማወቅ ችለናል። በተለይም የምስራቅ ሎንዶን ጋዜጣ በሰልፉ ላይ የተገኘችን አንዲት የኢሕአፓ አባል በዕለቱ ለምን እዚያ እንደተገኘች፣ የፖለቲካ አመለካከቷንና ሰላለዉ ሁኔታ በሚመለከት ቃለ መጠይቅ እንዳደረገላትና፣እርሷም በኢትዮጵያ ፖለቲካ ታሪክ ዉስጥ ጉልህ ድርሻ ያለዉና ለዴሞክራሲና ለኢትዮጵያ ብልፅግና በቀድምትነት የተደራጀዉ የኢህአፓ አባል እንደሆነችና አሁን ያለዉን መንግስት ገና ለስልጣን ከመቅረቡ በፊት ጀምሮ ዘረኛነቱን፣ ፀረ ህዝብነቱንና ፀረ ኢትዮጵያነቱን በመቃወም ለአፍታም እንኳ ያለመታከት እየታገለ ያለና የዛሬዉም ተቃዉሞ የዚሁ አካል መሆኑን በመግለፅ፣ የኢትዮጵያ ሕዝብ ባለፉት ተከታታይ መንግስታት ስቃዩን እንዳየና ኢሕአፓም በነዚህ መንግስታት ሁሉ እዉቅና እንደተነፈገዉ፣ እስካሁንም በአገር ዉስጥ በህቡዕ ብቻ እንደሚንቀሳቀስ፣ በርካታ አባሉትም እንደተሰዉበትና አሁንም በእስር እየማቀቁ መሆኑን፣ አሁን በስልጣን ላይ ያለዉ የወያኔ ዘረኛ መንግስት ምንም ኢትዮጵያዊነት እንደሌለዉና የዴሞክራሲ መብት በኢትዮጵያ እንደሌለ፣ ቢሮክራሲዉና የፀጥታዉ ኃይል በአንድ ዘር ቁጥጥር ስር ስለመሆኑ፣ በእርዳታ ስም ወደኢትዮጵያ የሚገባዉም ለዚሁ ጎጠኛ ቡድን ብቸኛ ጠቀሜታ እንጂ ለኢትዮጵያ ሕዝብ እንደማይደርስ፣ መንግስት ተብዬዉም በዘር ማጥፋት ወንጀል መጠየቅ እንደሚገባዉ ፣ በህጋዊ መንገድ እንዲንቀሳቀሱ የፈቀደላቸዉን የፖለቲካ ድርጅቶች መሪዎችንና አባላቱን እንደሚያንገላታና እንደሚያስር፣ ምስሏ የሚታየዉን ብርቱካን ሚዴቅሳን በምሳሌነት በመግለጽ በህጋዊ መንገድ የሚንቀሳቀስ የፖለቲካ ድርጅት መሪ እንደሆነችና በእስር ቤት እየማቀቀች መሆኗን ጨምራ በመግለፅ፣ ይህንን አረመኔ

መሪ ከነቡድኑ ለአለም ህብረተሰብ ለማጋለጥ ኢትዮጵያን በዚህ ቦታ እንደተሰባሰቡ ገለጻ አድርጋለታለች።

በዚህ የተቃዉሞ ሰልፍ ዕለትና የእንግሊዝ ባንክ በሚገኝበት አካባቢ ደግሞ በዋዜማዉ ኢሕአፓ የእንግሊዙ ጠ/ሚኒስቴር ጎርደን ብራዉን መለሰ ዜናዊን በስብሰባዉ ላይ መጋበዙ አሳፋሪ ነዉ የሚለዉ በእንግሊዘኛ የተዘጋጀዉ መግለጫ ለዉጭ ዜጎች፣ዴሞክራሲያ ደግሞ ለኢትዮጵያኑ የተበተኑ ሲሆን በእንግሊዘኛ ቋንቋ የተዘጋጀዉ የኢትዮጵያ የፖለቲካ እስረኞች አንድነት ኮሚቴ መግለጫም ደግሞ በድርጅቱ ደጋፊዎች ለዉጭች ዜጎች በስፊዉ ተሰራጭቷል። አንዳንድ የአፍሪካ አገር ዜጎች ከኢትዮጵያ እስረኞች አንድነት ኮሚቶ ጋር በመተባበር ኢሰበአዊ መንግስታትን ለማጋለጥና ለመቀራረብ ሀሳብ ማቅረባቸዉን ዘጋቢያችን ጨምሮ ገልጾልናል።

ባጠቃላይ ዕለቱ መለሰ ዜናዊ ሀፍረት የተከናነበበትና ደጋፊዎቹም አንገታቸዉን የደፉበት ቀን ለኢትዮጵያ ሕዝብ ደግሞ የምስራች እንደነበረ ዘጋቢያችን ከስፍራዉ ልኮልናል።

የመለስ ዜናዊ ቅሌት በለንደን ከተማ በመጋለጡ አምባገነኑ አቅዶት የነበረውን የፕሬስ ገለፃ መሰረዝ ተገደደ ::አፍሪካን ወክሎ በጉባዔው ይገኛል የተባለው ግብዝ አምባገነን ወተት እንደሰረቀች ድመት አንገቱን ደፍቶ በበለፀጉት ሀገሮች ጉባዔ ላይ ሲሽለኮለክ መገኘቱም ተዘግቧል፡፡ የአሜሪካኑን ፕሬዚዳንት እጅ ሲጨብጥ፤ ንግስት ኤልሳቤጥ ባደረገችው ግብዣ ሲገኝ ፊልሞችን በማሳየት መለስ ዜናዊ ቁም ነገር የሰራ ለማስመሰል ወያኔዎች ደፋ ቀና ቢሉም አንኳን አፍሪካን ራሱንም ሊወክል አለመቻሉ ተዘግቧል፡፡ በርካታ ኢትዮጵያውያን ተቃዋሚዎች ተሰልፈው መለስ ለፍርድ ይቅረብ ብለው ሲጮኹ መስማት የተገደደው አረመኔ ቀልቡ ተገፎ መቆየቱንና ተሰብሳቢዎቹም ቢሆኑ ከመጤፍ እንዳልቆጠሩት ለማወቅ ተችሏል፡፡ መለስን በመደገፍ ይሰለፋሉ የተባሉ ት ቅጥረኞችም ደፍረው ሊሰለፉ አልቻሉም፡፡ በአጭሩ በለንደኑ ጉባዔ መለስ ዜናዊ ሀፍረትን ተከናንቦ ተሸኝቷል ማለት የሚቻል ነው፡፡

ሁሉን በእሌ ሁሉን በመዳፌ ስር ባዩ የወያኔ አገዛዝ የቡና ንግድን በሰበብ አስባቡ በራሱ ቁጥጥር ስር ለማስገባት እርምጃ ከወሰደ በኋላ አሁን ደግሞ ይባስ ብሎ ከ 20 ሺ ያላነሱ የከተማ ፅዳት ሰራተኛ ሴቶችን ከስራና ከገቢ ለመማነጠል በራሱ ተቋም አማካኝነት አዲስ መመሪያ ህግ አውጥቶ መንቀሳቀስ መጀመሩን ሰራተኞቹ ሴቶች አጋልጠዋል፡፡ በፅዳት ስራ የተሰማሩት ሴቶች በአዲሱ ህግ መሰረት ከሰርሮ የሚፈናቀሉ መሆናቸውን ቢገልፁም በመመሪያው ማርቀቅም ቢሆን ድምፃቸው ያልተሰማ መሆኑን ጠቁመዋል፡፡ ወያኔ በሰበብ አስባቡ ሰራቶውን ሕዝብ እያጠቃ የራሱን ቁጥጥር በትንሹም ሆነ በትልቁ ተገቢ መስክ ላይ ሊያሰፍን መነሳቱን የፅዳት ሰራቶቅች ሰቆቃ ያጋልጠዋል ተብሏል፡፡ የኢትዮጵያን ቡና ጃፓን አልገዛም ያለችበት ምክንያት በቡናው ላይ የ ተባይ መግደያ መድህኒት ርዝራዥ በመገኘቱ መሆኑ ሲታወቅ ወያኔ ማዳበሪያ፤ ተባይ መግደያ፤ ሰው ሰራሽ ዘር እያለ በሚያሰራጨው ሁሉ የኢትዮጵያ መሬትና የአርሻ ምርት እየተጎዳ መሆኑ ተጋልጧል፡፡

ለጅቡቲ 70 ሜጋዋት የኤሌክትሪክ ሀይል እያቀረበ ያለው ወያኔ በከተሞች መብራት ሀይል በፈረቃ እያደለ መሆኑ ሲታወቅ በግልገል ግቤ እሰራዋለሁ ብሎ የጀመረው ግድብና ሀይል ማመንጫን በተመለከተ ዋና ተጠቃሚ ይሆናሉ ተብሎ የተገመተው የኬንያ መብራት ሀይል በጉዳዩ የለንበትም ሲል በይፋ ገልጧል፡፡ ግልገል ጊዜ ግድብ በደቡብ ኢትዮጵያ ያለውን የአካባቢ ሁኔታ ከመጉዳቱ ሌላ የኬንያን የቱርካና ሀይቅ የሚያደርቅ ነው ተብሎ ተወግዟል፡፡ ይህን የብዙ መቶ ሚለዮን ደላር ስራ የተኮናተረው የጣሊያኑ ሳልኮስት ኩባንያ አንድተለመደው ለወያኔ ባለስልጣኖች ብዙ ሚሊዮን ዶላር ጉቦ መስጠቱንም አንዳንድ ውስጠ አዋቂዎች አጋልጠዋል፡፡

በኢትዮጵያ የሀሰት ብርና የአሜሪካን ዶላር ሲሰራጭ ያዝኩ ብሎ የወያኔ ፖሊስ ተቋም ባለፈው ሰሞን ይፋ ያደረገውን ዜና በተመለከተ በሀገሪቷ የሀስት ብር ኖቶች በተለይም በገጠር ሲሰራጭ ለብዙ ዓመታት የቆየ መሆኑን ያሀጋለጡ ክፍ.ሎች ይህ ተግበናር በወያኔ በራሱ ሲካሄድ የቆየ ነውብለው ጠቁመዋል፡፡ የኢትዮጵያ ብር በፈረንሳይ ሲታተም ቆይቶ በአሁኑ ጊዜ በአንግሊዝና

በጀርመን የሚታተም ሲሆን የሀሰት ብሮችን የወያኔ ባለስልጣኖች ቀደም በኬንያ አሁን ግን ይበልጥ በረቀቀ መንገድ በጃፓን እያሳተሙና በሀገር አስገብትው እያሰራጩ መሆኑ ታውቋል፡፡ ፖሊሶቹ ያዝን የሚሉት የግለሰብ ተፎካካሪዎችን እንጂ ዋነኞቹ የሀሰት ብር አስገቢዎች ወያኔዎ ች ማንም የሚነካቸው አልሆኑም ተብሏል፡፡ በፈረንሳይ የሚታታመው የኢትዮጵያ ፓስፖርትም በወያኔ ባልስልጣኖች በውስጥ ውስጥ ለጎረቤት ሀገር ዜጎች እየተሸጠ መሆኑንም ለማወቅ ተችሏል ፡፡በተያያዘ ዜና አንድ የአሜሪካ ብር በ13 ብር ከህምሳ መመንዘር መጀመሩን ለማወቅ ተችሏል.

ባለፈው ሰሞን የመለስ ዜናዊ ሚስት አዜብ ጎላ የወያኔ የኤኮኖሚ ተቋም የኤፈርት ወይም የ ትእምት ምክትል ሃለፊ ሆኗ መሾሟ መለስ ዜናዊ የሀገሪቷን ሀብት በቀጥታ በራሱና በቤተሰቡ እጅ ለማስገባት መወሰኑን ያሳያል ተብሏል፡፡ በ ትእምት ስር ከሀያ ባለይ ኩባንያዎች የሚተዳደ ሩ ሲሆን ተቋሙ የሀገሪቷን ኤኮኖሚ ከሳውዲው ቱጃር ጋር. ተያይዞ እየተቆጣጠረ መሆኑ የሚታወቅ ነው፡፡ ከአዜብ በላይ በዋና ሀላፊነት የተመደበው አባዲ ዘሞ የመለስ ሎሌ ከመሆኑ ሌላ ከአዜብ ትዕዛዝ የሚወጣ አለመሆኑ ሲነገር የኤፈርት አለቃ የነበረው ስብሀት ነጋ መወገዱ አዜብ ከስብሀት ጋር በጀመረችው ግብግብ የበላይነትን እየያዘች መምጣቷን ይጠቁማልም ተብሏ ል፡፡ ስብሀት ነጋ ቀስ በቀስ ከስልጣን እየተፈናቀለ ሲሆን ከነጋዴዎች ጋር ተጣምሮ የተሰማራበት የሙስና ሜዳም እየጠበበበት መምጣቱን ያሳያል፡፡ በሰካራምነት የሚታወቀው ስብሀት ነጋ በአዜብ ሲጠቃ በዝምታ ይቀበላዋል ወይስ መለስ ላይ የተዋቀበትን ሴራና ተንኮል ይሸርባል የሚለው ጥያቄ ገና ምላሽ አላገኘም ሲሉ ታዛቢዎች ያቀርባሉ፡፡